15/11/2000 ዓ.ም

<u>ለርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረጽዮን ቅ/ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤተክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት።</u>

<u>ለንደን።</u>

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናንተ ጋር ይሁን፤ በማለት የአክብሮት ሰላምታችንን እናቀርባለን።

የደብራችን የካህናት ጉባዔ፡ ቤተክርስቲያናችን ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/አብያተክርስቲያናት ጋር ስለሚኖራት ግንኙነትና አባቶች ካህናትና ጳጳሳት በእን ግድነትም ሆነ በግብዣ ወደ ቤተክርስቲያናችን ቢመጡ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን ሁኔታ አስመልክቶ በሰፊው ተወያይቶበታል።

ጉባኤው 3 አዘጋጅ አባላትን መርጦና ሰፋ ያለ ጊዜ ወስዶ በመወያየት የተስማማበትን ቃለ ጉባኤ ከዚህ የመሸኛ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆናችንን በአክብሮት እንገልጻለን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር።

ዲ/ድርሻዬ ለማ።
የዕለቱ የካህናት ጉባኤው ቃለ ጉባኤ አዘጋጅ አባልና ጸሐፊ።

<u>ግልባጭ ፤</u>

ለሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ
ለቁጥጥር ኮሚቴ
ለሕንፃ ቤ/ክና ልማት ኮሚቴ
ለሰንበት ት/ቤት የአመራር ኮሚቴ

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional
A-PDF Merger DEMO : Purchase from www.A-PDF.com to remove the watermark

**<u>የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፣ የካህናት ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ።</u>**

<u>የስብሰባ ቦታ ፤ የደብሩ ጽ/ቤት</u>
<u>ቀን ፤ 15/11/2000 ዓ.ም.</u>
22-07-2008

<u>በስብሰባው የተገኙ አባላት ፤</u> <u>ፊርማ ፤</u>

1. ቆሞስ አባ ግርማ ከበደ
2. መሪጌታ ዓለማየሁ ደስታ
3. መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት
4. ቄስ ገበዝ መስፍን ሠምረ
5. ቀሲስ ሙሉብርሃን ስዩም
6. መሪጌታ መረሐጽድቅ ቀናው
7. ሊ/ዲ/ ተረፈ አካሉ
8. ሊ/ዲ/ ዳዊት ገ/ዮሐንስ
9. ሊ/ዲ/ ዳዊት ደንበሩ
10. ዲ/እስራኤል አስፋው
11. ዲ/ዮርዳኖስ ወ/ሰንበት
12. ዲ/የማነ ወልዴ
13. ዲ/ሳምሶን ጫላ
14. ዲ/አባተ ጎበና
15. ዲ/ደረጀ ሞገስ
16. ዲ/ድርሻዬ ለማ
17. ዲ. ካሣሁን ተሰማ
18. __________
19. __________
20. __________

<u>አጀንዳዎች ፤</u>

የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፣

1) የውስጥ አስተዳደሯንና *ከእናት ቤ/ክን (ቅዱስ ሲኖዶስ) ጋር ያላትን ግንኙነት በሚመለከት ፤*
2) ከሌሎች የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት ጋር የሚኖራትን ግንኙነት በሚመለከት ፤
3) የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት አገልጋይ ካህናት (አባቶች ጳጳት) በእንግድነትም ሆነ በግብዣ ቢመጡ ፣ አገልግሎት (ትምህርት) ሊሰጡ ስለሚችሉበት ሁኔታ ፤
4) ደብረ ገነት ቅደስት ሥላሴ በሚል አዲስ ቤተክርስቲያን ሲቋቋም ፤ ከዚህም ከዚያም እያልን አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉ ካህናትንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን አስመልክቶ ፣ በካህናት ጉባኤው የተሰጠውን ጊዜያዊ ውሳኔ በሚመለከት የቀረቡ ናቸው።



Created with
nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

1.) <u>የቤተክርስቲያናችን የውስጥ አስተዳደሯንና ከእናት ቤ/ክን (ቅዱስ ሲኖዶስ) ጋር ያላትን ግንኙነት በሚመለከት ፤</u>

የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣ ፓትርያርክ አባ ጳውሎስን አስመልክቶ በ2/5/1998 ዓ.ም ባወጣችው የአቋም መግለጫ መሠረት ፤ የፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ስም ባለመጠራቱ ምክንያት አንዳንድ ካህናትና ምእመናን ቤተክርስቲያናችን ከእናት ቤተክርስቲያን (ቅዱስ ሲኖዶስ) እንደተለየች አድርገው በማሰባቸውና ፣ ምእመናንን ግራ ሊያጋቡ እንደሚችሉ የካህናት ጉባኤው ተገንዝቦ ፤ የቤተክርስቲያናችንን የአቋም መግለጫውንና የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡን በድጋሚ ጠቅሶ ማረጋገጡ አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል።

ስለሆነም ፤ የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፣ በውስጥ መተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 2 (1) እና በ2/5/1998 ዓ.ም በወጣው አቋም መግለጫ ተራ ቁ. 1. ገጽ 8 እና ተራ ቁ. 7. ገጽ 10 ላይ በግልጽ እን ደተቀመጠው ፤ ቤተክርስቲያናችን አሁንም ሆነ ለወደፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እናት ቤተክርስቲያን አካልና ፣ በአንድ ቅዱስ ሲኖዶስ ስር የምትመራ መሆኗንና ፤ እንዲሁም የውስጥ አስተዳደሯም ፣ ሰኔ 1998 ዓ.ም በጠቅላላው የሰበካው መንፈሳዊ ጉባኤ በጸደቀውና በወጣው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መሆኑን የካህናት ጉባኤው በድጋሚ ያረጋግጣል።

<u>2. የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፣ ከሌሎች የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት ጋር የሚኖራትን ግንኙነት በሚመለከት ፤</u>

የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፣ የውስጥ መተዳደሪያ ደንቧንና አቋሟን ጠብቃ ፤ ከሁሉም የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት ጋር በመተባበር ፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነታችን እንዲስፋፋና መንፈሳዊ አገልግሎት ለሁሉም ምእመናን እንዲዳረስ የማድረግ አቋሟ የጸና መሆኑን የካህናት ጉባኤው በድጋሚ ያረጋግጣል።

*<u>3. የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት አገልጋይ ካህናት (አባቶች ጳጳት) በእንግድነትም ሆነ በግብዣ ወደ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤ/ክን ቢመጡ ፣ መንፈሳዊ አገልግሎት (ትምህርት) ሊሰጡ የሚችሉበትን ሁኔታ በሚመለከት ፤</u>*

ቀኖና ቤ/ክርስቲያናችንን ጠብቀው በሌሎች የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት ያገለገሉና የሚያገለግሉ ፣ ካህናትና አባቶች ጳጳሳት (እኔ የጴጥሮስ ወይም እኔ የአጵሎስ የሚል አመለካከት ቢኖራቸውም ፤ በእንግድነት ወይም በግብዣ ወደ ቤ/ክርስቲያናችን ቢመጡ ፣

ሀ.) የክህነት ስልጣናቸውና ሙያቸው በሚፈቅድላቸው መሠረት ቀድሰው መቁረብ/ማቁረብና ፣ ወንጌለመንግስትን መስበክ ፣ ሃይማኖታዊና ክህነታዊ መብትና ግደታቸው መሆኑን ቤተክርስቲያናችን ታረጋግጣለች።

ለ.) ማንኛውም ካህን ወይም አባት በቤ/ክናችን መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ ፣ የቤተክርስቲያናችንን ፣ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና አቋም የማክበር ግዴታ ይኖርበታል። በዚህም መሠረት ፤ የአባ ጳውሎስንም ሆነ የአባ መርቆርዮስን ስም በማንኛውም ሥርዓት



Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ጸሎት ላይ መጥራት የለበትም። እንዲሁም ፤ ለስብከተ ወንጌል ወይም ለመንፈሳዊ ትምህርት ቢጋበዝ ፣ ንጹህ የሆነ ትምህረተ ወንጌልን ከማስተላለፍ (ከመስጠት) ውጪ ፣ አንዱን የሚያስደስትና ሌላውን የሚያሳዝን መልእክት ማስተላለፍ የለበትም። ይሁን እንጂ በእንግድነት የሚመጡት ካህን ወይም አባት ፣ ለቅዳሴ ወይም ለስብከት ከመጋበዛቸው በፊት ፣ የደብሩ ጽ/ቤትና የካህናት አስተዳደር ጉባኤው ማወቅና በቅድሚያ የቤተክርስቲያናችንን ሥርዓትና ደንብ የማስረዳትና የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት።

ሐ.) በእንግድነት ወይም በግብዣ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ የተሳተፉት ካህን ወይም አባት ፣ ከላይ በተገለጹት የቤተክርስቲያናችን ኃላፊዎች የተሰጣቸውን የደብሩን የውስጥ ሥርዓትና ደምብ ተላልፈው ቢገኙ ፤ ጉዳዩ በአስቸኳይ ለጠቅላላው የካህናት ጉባኤ ቀርቦ ፣ አስፈላጊው ውሳኔ እንዲሰጠው ይደረጋል።

መ.) ከብሪታንያ ውጭ የሚኖሩ ካህንን ወይም አባትን መጋበዝን በሚመለከት ግን ፤ በቅድሚያ የግብዣው አስፈላጊነት በጠቅላላው የካህናትና በሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጥምር ጉባኤ ሲታመንበት ብቻ መሆን እንዳለበት የካህናት ጉባኤው አምኖበታል።

ሠ.) የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ነኝ በሚል የመጡትን ብጹእ አቡነ እንጦንስን በሚመለከት ግን ፣ ከዚህ በፊት በጥምር ጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ እንደተጠበቀ መሆኑን ጉባኤ አያረጋገጠ ፤ ለወደፊት እንደገና ማየት አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝም እንኳን ፣ በዚያው በጥምር ጉባኤው መታየት የሚገባው መሆኑን የካህናት ጉባኤው አመኖበታል።

4. <u>ደብረ ገነት ቅደስት ስላሴ በሚል አዲስ ቤተክርስቲያን ሲቋቋም ፣ ከዚህም ከዚያም እያልን አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉ ካህናትንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን አስመልክቶ ፣ በካህናት ጉባኤው የተሰጠውን ጊዜያዊ ውሳኔ በሚመለከት ፤</u>

በቤተክርስቲያችን የካህናት ጉባኤውም ሆነ በሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ዘንድ ምክክርና ውይይት ሳይደረግበት ፣ በፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ላይ የቤተክርስየቲያናችን ካህናትና ምእመናን በአንድነት የወሰዱትን አቋም በመቃወም ፤ ብፁዕ አቡነ ሙሴ እና የተወሰኑ ካህናት አዲስ ቤተክርስቲያን ከመክፈታቸውም በላይ ፤

1. አዲሱን ቤተክርስቲያን ሲከፍቱ ፣ በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤ/ክን ፈቃድና እውቅና የተከፈተ በማስመሰል ምእመናንን ግራ የሚያጋባ ተግባር በመፈጸማቸው ፤
2. ከቤተክርስቲያናችን ፈቃድና እውቅና ሳይኖራቸው ከለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ጋር አንድ ነን በማለት በቤተክርስቲያናችን የህንጻ ግዥ ስም የገንዘብ እርዳታ በመጠየቃቸው ፤
3. ይህንንም ኃሳባቸውን ለማሳካት ፣ ብፁዕ አባ ሙሴና አብረዋቸው ያሉ ካህናት አልፎ አልፎ ወደቤተክርስቲያናችን በመምጣትና አንድነት እንዳላቸው በማሳየት ፣ ምእመናኑን ግራ ለማጋባት የተጠቀሙበትን ዘዴ ለመግታትና ፤ አዲስ የተከፈተውም ቤተክርስቲያን ዓላማው ምን እንደሆነ እስኪጣራና ሁኔታው ግልጽ እስከሚሆን ድረስ ፣ በቤተክርስቲያናችን በግንባር የሚያገለግሉ ካህናትና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች አዲስ ተከፈተ ወደሚባለው ቤተክርስቲያን ሄደው አገልግሎት እንዳይሰጡ ፤ እንዲሁም ፤ አዲስ ቤተክርስቲያን ከፈትን የሚሉትም ካህናት ወደኛ ቤተክርስቲያን መጥተው



Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

አገልግሎት እንሰጣለን እንዳይሉ በሚል የካህናት ጉባኤው ጊዜያዊ ውሳኔ ማስተላለፉ ይታወሳል።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በወቅቱ የካህናት ጉባኤው ያስተላፈው ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም ፤ እስከ አሁን ድረስ ሁኔታው ተጣርቶና በወቅቱ የተወሰነው ውሳኔ ዘለቄታዊ የሆነ መፍትሄ እንዲኖር ባለመደረጉ ፤ ከቤተክርስቲያናችን ሳይለዩ ወደ አዲሱ ቤተክርስቲያን ሄደው ለማገልገል የሚፈልጉ ካህናትና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን ግራ ሊያጋባ የሚችል ሁኔታን መፍጠሩን የካህናት ጉባኤው ተገንዝቦታል።

ስለዚህ ፤ ደብረ ገነት ቅደስት ሥላሴ በሚል አዲስ ቤተክርስቲያን ሲቋቋም ፣ ከዚህም ከዚያም እያልን አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉ ካህናትንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን አስመልክቶ ፣ በካህናት ጉባኤው የተሰጠው ጊዜያዊ ውሳኔ ፣ በዚህ ውሳኔ የተነሳ መሆኑን የካህናት ጉባኤው አያረጋገጠ ፤ በአፈጻጸም ላይ የሚከተሉት መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ በአንድ ድምጽ ወስኗል።

ሀ.) በቅድሚያ በዚህና በተለያዩ ምክንያቶች ቅሬታ ኑሩዋቸው እራሳቸውን ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ያስገለሉ ወይም አንዱ ከሌላው ጋር ቅሬታ ይዞ የሚኖር ካለ እርስ በእርስ ተወቃቅሶ ሁሉም በፍቅርና በአንድነት ሥርዓቱንና ህጉን ጠብቆ ፤ አቅሙ ፤ ችሎታውና ጊዜው እንደፈቀደለት ቤተክርስቲያንን ሊያገለግል እንዲችል የካህናት ጉባኤው አንድ የእርቀሰላም ጉባኤ ጠርቶ በመወያየትና በመመካከር ቅሬታዎች እንዲወገዱና እርቀሰላም እንዲወርድ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል። በመቀጠልም ፤ በካህናቱና በሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ፣ እንዲሁም በሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች በሚያገለግሉ ምእመናን መካካል የእርቀሰላም ጉባኤ እንዲደረግ ተወስኗል።

ለ.) ከደብረገነት ቅድስት ሥላሴም ሆነ ከሌሎቹ የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት ወደ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚመጡ ካህናት ሁሉ ፣ ከዚህ በላይ በተራ ቁ. 3 እንደተገለጸው በ2/5/1998 ዓ.ም በፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ላይ የወጣውን የአቋም መግለጫ የማክበር ግዴታ ይኖርባቸዋል።

ሐ.) የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ ካህናት በማንኛውም የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት ቀድሶ መቁረብ/ማቁረብና ፣ ትምህርተ ወንጌል መስጠት ፣ ክርስቲያናዊና ክህነታዊ መብትና ግደታቸው በመሆኑ ፤ በደብረገነት ቅድስት ሥላሴም ሆነ ፣ በሌሎቹ የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት በመሄድ ማገልግል ይችላሉ።

መ.) የቤተክርስቲያናችን የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ወደ ደብረገነት ቅ/ሥላሴም ሆነ ወደሌሎቹ የኢ/ኦ/ተ አብያተክርስቲያናት እየሄዱ ፤ ወይም ሌሎቹን የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ወደ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመጋበዝ ፣ በአንድነት መዘመርና ማገልገል የቤተክርስቲያናችን ተቀዳሚ ተግባር መሆኑን የካህናት ጉባኤው ተገንዝቦ ፤ ከዚህ ቀደም ፣ የደብረገነት ቅ/ሥላሴ ቤተክርስቲያን በተከፈተበት ወቅት ፣ ተፈጥረው የነበሩ ችግሮችን ለማስተካከል ሲባል በካህናት ጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ ፣ ከላይ እንደተገለጸው በዚህ ውሳኔ የተነሳ መሆኑን ለሰንበት ት/ቤቱ እንዲተላለፍ ወስኗል።



Created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

በአጠቃላይ ፤ በአፈጻጸም ላይ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ እንዳይፈጠርና ፣ የካህናት ጉባኤውም ውሳኔ ቀኖና ቤተክርስቲያንን ፣ የውስጥ መተዳደሪያ ደንባችንንና የአቋም መግለጫችንን የተከተለ መሆኑን በግልጽ ለማሳወቅ እንዲቻል ፤ ይህ ውሳኔ በጽ/ቤቱ በኩል ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ እንዲቀርብ ሆኖ ፤ በግልባጭ በቤተክርስቲያናችን መዋቅር ውስጥ ላሉት ለሁሉም ንዑሳን ኮሚቴዎችና የመንፈሳዊ አገልግሎት ክፍል ኃላፊዎች እንዲደርሳቸው ተወስኗል። ከዚህ ሌላ ፤ ማብራሪያና ውይይት የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ አንድ የውይይት ጉባኤ መጥራት የሚቻል መሆኑን በማረጋገጥ ፤ የካህናት ጉባኤው የዕለቱን ስብሰባ በጸሎት ዘግቷል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

<u>ግልባጭ ፤</u>

1. ለደብሩ ሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ ፤
2. ለደብሩ ቁጥጥር ኮሚቴ ፤
3. ለደብሩ ሕንጻ ቤ/ክንና ልማት ኮሚቴ ፤
4. ለደብሩ የሰንበት ት/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ።



Created with
nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional